## እይታዬ

በዚህ ዓምድ ማንኛውም ግለሰብ በፈለገው ጉዳይ ላይ በሚመቸው መንገድ አስተያየቱን መጻፍ ይችላል በዚህ ዓምድ ላይ የሚወጡ ጽሑፎች የዝግጅት ክፍሉ ኀሳብ ተደርገው መወሰድ የለባቸውም::

# የዓባይን ልጅ ውሃ ጠማው ብረት ወርቅ ከሆነ ውሃ ቤንዚን ቢሆንስ?

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደ ማርያም
የካቲት 2000

የቤት ኪራይ ለመክፈል ሰውላኩሁ፤ የቤቱ ኪራይ ከመከፈሉ በፊት የውሃ አገልግሎት መከፈል አለበት ተባለ፤ ለምን የውሃው ቅድሚያ እንደተሰጠው ብዙ ሊያነጋግር ይችላል፤ የአስተሳሰብ ችግር እንዳለበት ግን አያከራክርም:: ከዚህ በፊት እንዲህ ያለ አሠራር አጋጥሞኝ አያውቅም፤ እንዲያውም ኪራይ ተቀባዮቹ በጣም ቀልጣፋዎች ናቸው:: ለማናቸውም የውሃው ሂሳብ ከመጋቢት 1999 ጀምሮ እስከ መስከረም 2000 ዓ.ም ተብሎ የተጠየቀው 1,617,04 (አንድ ሺህ ስድስት መቶ አስራ ሰባት ብር ከዜሮ አራት ሳንቲም) ተከፈለና የቤት ኪራዩ ሳይከፈል ቀረ::

የውሃ ክፍሉን የአሠራር ግድየለሽነት ለማመልከት ያህል በተባለው ጊዜ ውስጥ እኔ ውሃ በነፃ በምጠቀምበት በቃሊቲ ነበርሁ፤ ስለዚህ ሳንቲም ድረስ የተሰላው ሂሳብ ከአስመሳይነት በላይ ምንም እውነት የሌለበት ነው:: በቤቱ ውስጥ ብኖርና በውሃም ብጠቀም ስንት ሜትር ኩብ ውሃ በቀን ተጠቀምሁ? ውሃውስ በሜትር ኩብ ምን ያህል ያወጣል? ለሚሉት ጥያቄዎች ደረሰኙ መልስ አይሰጥም፤ በየትኛውም ሱቅ ገብተን ዕቃ ስንገዛ በደረሰኙ ላይ ዝርዝር መረጃ ይኖራል:: በተሰጠኝ የውሃ የጅምላ ሂሳብ ግን ለአንድ መቶ ሰማንያ ቀኖች የውሃ አገልግሎት ያስከፈሉኝ 1617.04 ብር ምንም ዝርዝር ማስረጃ የለበትም:: እኔ ሳሰላው ግን በቀን ለውሃ የሚያስከፍሉኝ 8.98 ሳንቲም ወይም ከአንድ ሊትር ቤንዚን ዋጋ ጋር የተቃረበ ነው ማለት ነው:: ከአንድ የአሜሪካ ብርም ብዙ አይርቅም::

> **የውሃ ክፍሉን የአሠራር ግድየለሽነት ለማመልከት ያህል በተባለው ጊዜ ውስጥ እኔ ውሃ በነፃ በምጠቀምበት በቃሊቲ ነበርሁ፤ ስለዚህ ሳንቲም ድረስ የተሰላው ሂሳብ ከአስመሳይነት በላይ ምንም እውነት የሌለበት ነው:: በቤቱ ውስጥ ብኖርና በውሃም ብጠቀም ስንት ሜትር ኩብ ውሃ በቀን ተጠቀምሁ? ውሃውስ በሜትር ኩብ ምን ያህል ያወጣል?**

በእኔ ከፍ ያለ ግምት በቤቱ ውስጥ ብኖር በቀን ሁለት ሜትር ኩብ ውሃ ብፈጅ በስድስት ወራት ውስጥ 60 ሜትር ኩብ ውሃ ተጠቅሜአለሁ ማለት ነው:: በከፈልሁት የውሃ ክፍሉ ስሌት መሠረት በወር 269.51 (ሁለት መቶ ስድሳ ዘጠኝ) ከፍያአለሁ፤ በእኔ ስሌት ደግሞ በሜትር ኩብ 4.50 ቢታሰብ (የውሃ ክፍሉ በቀን ዘጠኝ ብር ስለወሰነብኝ) በወር 270 ብር፤ በቀን ዘጠኝ ብር ይሆናል፤ የአንድ ሊትር ቤንዚን ዋጋ ለመሆን ስድሳ ሳንቲም ይቀረዋል:: እንዲህ ያለ የውሃ ዋጋ በረሀ በሆኑ አገሮች እንኳን የሚጠይቅ መንግሥት የሚባል ድርጅት ያለ አይመስለኝም:: ዱሮ በወር 25 ብር ለውሃ ስንጠየቅ እናማርር ነበር!

ከኪራይ ቤቶች አስተዳደር እንደተገነዘብሁት የውሃ ክፍል ጅምላ ክፍያ ይልክላቸዋል፤ ያንን ጅምላ ክፍያ ለአፓርትመንት ነዋሪዎች የሚያካፍሉት በእያንዳንዱ ቤት ውስጥ በሚኖሩት ነዋሪዎች ብዛት ሳይሆን ቤቱ ውስጥ ባለው የመኝታ ቤት ቁጥር ነው! በውሃ የሚጠቀሙት መኝታ ቤቶች ናቸው? ወይስ ሰዎች? አንድ መኝታ ቤት ባለው ቤት ውስጥ ከአምስት የማያንሱ ሰዎች የሚኖሩበት አውቃለሁ፤ ሁለት መኝታ ቤቶች ባሉት ውስጥ አንድ ሰው ብቻ ይኖራል፤ ታዲያ እንዴት ነው በመኝታ ቤቶች ቁጥር የውሃ ፍጆታ ሊሰላ የሚቻለው? ለውሃ የሚከፈለው ስሌት በሜትር ኩብ ስንት ብር ታስቦ እንደሆነ የኪራይ ቤቶች አያውቅም:: የውሃ ክፍል ኃላፊዎች የአንድ ወር የውሃ ሂሳብ ከመብራት ኃይል ክፍያ ሲበልጥ፣ እንዲያውም ከቤቱ ኪራይ ሲበልጥ፣ አንድ የተሳሳተ ስሌት ማድረጋቸውን ለመረዳት አልቻሉም ማለት ነው:: ከፍ ያለ የአስተሳሰብ ችግር መኖሩ ግልጽ ነው::

በኢትዮጵያ ውሃ ይህን ያህል የተወደደው እድገታችን በመፋጠኑ የተነሣ በውሃ የሚጠቀሙ ሰዎች በጣም ስለበዙ ነው (ዱሮ ያለውሃ ይኖሩ እንደሆነ)? ወይስ ከባድ የውሃ እጥረት ስላለ ነው? ወይስ የአሜሪካ የውሃ እርዳታ ስላልተጠየቀ ነው? ወይስ ኃላፊዎች ተብለው የሚሾሙት ሰዎች ችሎታ አራት መደብ ደረጃ ገና ያልደረሰ ነው? ወይስ የግዴለሽነት አሠራር ነው? እነዚህ የደረደርሁአቸው ጥያቄዎች መመሪያ ተቀጥቶአቸው በዚያ መሠረት የሚሠሩትን ተራ ሠራተኞች አይመለከትም፤ እነሱ



የታዘዙትን ፈጻሚዎች ናቸው:: ጥያቄዎቹ የሚመለከቱት መመሪያውን ለማውጣት ሥልጣን ያላቸውን ነው::

አገሉ ዓይነት እድገት ገጥሞን እስካሁን የምግብና የመኖሪያ ችግር ማስከተሉን በሐዘንና በትካዜ እየቻልነው ቆየን፤ አሁን ደግሞ በውሃ መጣብን፤ ነገ በምንተነፍሰው አየር ይመጣብን ይሆን? የኢትዮጵያ ነፃ ገበያ ነፃ ነገር አያውቅም ማለት ይሆን?

በእውነት የመንግሥት ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች ይህንን ያህል ለውሃ ይከፍላሉ? በየትም አገር ቢሆን ውሃ በጣም ርካሽ ነው፤ ምክንያቱም ለጤንነትና ለጤናማ ኑሮ አስፈላጊ በመሆኑና በውሃ አዘውትሮ በመጠቀም በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችል መሆኑ ነው:: ለተራው ዜጋ ማሰብ ዘመን ያለፈበት አሠራር የሆነ ይመስላል::